ኢሰመጉ
EHRCO

# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው፡፡
EHRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.

ጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም

## ለጎሣ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ ይሰጥ
## 106ኛ ልዩ መግለጫ

### መግቢያ

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው በህይወት የመኖርና የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችዉ የሲቪልና የፓለቲከ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ ይህንኑ መብት አረጋግጦ መንግስታት በቃልኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው በአንቀጽ 2(1)(2) ይደነግጋል፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስትም በአንቀጽ 14 ላይ «ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው» በማለት ይደነግጋል፡፡

በአገራችን እነዚህ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች በተለያዩ ምክንያቶች እየተጣሱ ይገኛሉ፡፡ በተለያዩ ብሄረሰብ አባላት መካከል የሚነሱ ግጭቶች በዚህ በኩል ጉልህ ድርሻ አላቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) በዚህ 106ኛ ልዩ መግለጫው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በሚኖሩ የኮይራ ብሄረሰብ አባላት እና  በአዋሳኙ በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን አባያ ገላና  ወረዳ በሚኖሩ የጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት መካከል በተከሰተ ግጭት የደረሰውን የህይወት ጥፋት፣ የንብረት ውድመትና የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች በቦታው በመገኘት አጣርቶ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

### ዝርዝር

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በሚኖሩ የኮይራ ብሄረሰብ አባላት እና  በአዋሳኙ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጉጂ ዞን አባያ ገላና ወረዳ በሚኖሩ የጉጂ ኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት መካከል ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት በተፈጠሩ ግጭቶች ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ጥፋት መድረሱን ኢሰመጉ በየጊዜው አሳውቋል፡፡ ለምሳሌ ያህልም በመስከረም ወር 1999 ዓ.ም በተከሰተ ግጭት 11 ሰዎች ህይወታቸውን ሲያጡ 18 ሰዎች መቁሰላቸውንና ከፍተኛ  የንብረት  ውድመት መድረሱን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስለጉዳዩም በኢሰመጉ 98ኛ ልዩ መግለጫ ተዘግቧል፡፡

ይሁን እንጂ ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ባለማግኘቱ ከታህሳስ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ቀናት በተከሰቱ ግጭቶች አራት ሰዎች ህይወታቸውን ሲያጡ አምስት ሰዎች ደግሞ ቀላልና  ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡ በግጭቱ ሳቢያ ከፍተኛ

ንብረት ወድሟል። ሰላማዊ ሰዎች ከቀዬአቸው ተፈናቅለዋል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

**በግጭቱ የተገደሉ**

| ተ.ቁ | የተጎጂው ስም | ጾታ | ዕድሜ | ዝርዝር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ደላኔ ዲዶ | ወንድ | 55 | በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ቀበሌ ነዋሪ አርሶ አደር ነበሩ። ታህሳስ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት እግራቸውን በጥይት ተመተው ከ 4 ቀን በኋላ ሰውነታቸው ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ተቆራርጦ ሁለት እግራቸው ሲቀር ሌላው አካላቸው ጂጃላ እየተባለ በሚጠራው ቦታ ተገኝቶ ተቀብረዋል። |
| 2 | አዘነ አሊቶ | ወንድ | 45 | በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ቀበሌ ነዋሪ አርሶ አደር ነበሩ። ታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት በጥይት ጭንቅላታቸውን ተመተው ህይወታቸው አልፏል። |
| 3 | ምትኩ በኔቻ | ወንድ | 50 | በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ወረዳ ነዋሪ አርሶ አደር ነበሩ። ታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት ጀርባቸውን በጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፏል። |
| 4 | ሰለሞን ደነቀ | ወንድ | 43 | በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ቀበሌ ነዋሪና የጃሎ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ሀላፊ ነበሩ። ታህሳስ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በጉጂ ኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት በጥይት ሽንጣቸውን ተመተው ህይወታቸው አልፏል። |

**በግጭቱ የቆሰሉ**

| ተ.ቁ | የተጎጂው ስም | ዝርዝር |
|---|---|---|
| 1 | ተረፈ ተስፋዬ | በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ቀበሌ ነዋሪ አርሶ አደር ናቸው። ታህሳስ 20 ቀን 2000 ዓ.ም በጤፍ ማሳቸው ውስጥ እንዳሉ በተተኮሰባቸው 2 ጥይት እጅ እና እግራቸውን ተመተው በህክምና ላይ ይገኛሉ። |
| 2 | ሰንበቱ ኮራ | ነዋሪነታቸው በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጂጃሎ ቀበሌ ሲሆን ታህሳስ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በጥይት አንድ እጃቸውን ተመተው በህክምና ላይ ይገኛሉ። |
| 3 | አማሬ አስፋው | ነዋሪነታቸው በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ቀበሌ ሲሆን |

| | | |
|---|---|---|
| | | ታህሳስ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በጥይት እግራቸውን ተመተው በህክምና ላይ ይገኛሉ:: |
| 4 | ነፍሱ ጥላሁን | ነዋሪነታቸው በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ቀበሌ ሲሆን ታህሳስ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በጥይት ትከሻቸው ላይ ተመተው በህክምና ላይ ይገኛሉ:: |
| 5 | አበራ ሶዶታ | ነዋሪነታቸው በአማሮ ኬሌ ልዩ ወረዳ በጃሌ ቀበሌ ሲሆን ታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በጥይት ተመተው በሕክምና ላይ ይገኛሉ:: |

ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ ግጭት ንብረትነታቸው በአብዛኛው የኮይራ ብሔረሰብ አባላት የሆኑ 97 የሳር ክዳን መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል፣ 27 የቆርቆሮ ቤቶች ተነቃቅለው 538 ቆርቆሮዎች ተዘርፈዋል፣ 7 ጎተራ እህል ተቃጥሏል፣ 9 ክምር ጤፍና 1 ክምር አደንጓሬ ተቃጥሏል:: በተጨማሪም ህብረተሰቡ የሚገለገልበት 1 የእህል ወፍጮ ተነቃቅሎ ተወስዷል፣ እንዲሁም የጤና ኬላ፣ የግብርና ልማት ጣቢያ፣ የፖሊስ ፅ/ቤት፣ የቀበሌ ፅ/ቤት፣ የምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት የቴሌኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት ንብረቶች እና የጀሎ ትምህርት ቤት ንብረቶች ተዘርፈዋል አሊያም ተቃጥለዋል:: ለጊዜው ቁጥራቸው ያልታወቀ ከብቶችም ተዘርፈዋል:: በዚሁ ግጭት ከ 800 ያላነሱ አባወራዎች ከነቤተሰቦቻቸው አካባቢያቸውን ለቀው የተሰደዱ ሲሆን ትምህርት ቤቶችም ተዘግተዋል::

ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የአካባቢው ጸጥታ ያልተረጋጋ ሲሆን በተለይም በዋናነት ግጭቱ የተከሰተበት ቦታ በፌዴራል ፖሊስ አባላት እየተጠበቀ ይገኛል:: የአካባቢውን የመንግስት አመራር አባላት ጨምሮ ኢሰመጉ ያነጋገራቸው የአካባቢው ነዋሪዎች መንግስት ለጉዳዩ ዘላቂ መፍትሄ ካላበጀለት ግጭቱ እንደገና ሊያገረሽና ከዚህም የከፋ ችግር ሊከሰት እንደሚችል ያላቸውን ስጋት በመግለጽ ዘላቂ መረጋጋት እስከሚሰፍን ድረስ መንግስት ጥበቃ ሊያደርግላቸው እንደሚገባ ገልጸዋል::

## ማጠቃለያ

- ኢሰመጉ በሁለቱ ብሔረሰብ አባላት መካከል በተነሳው ግጭት ሳቢያ በኮይራ ብሔረሰብ አባላት ላይ የደረሰው ግድያና የአካል ጉዳት እጅግ ያሳዘነው መሆኑን እየገለጸ ድርጊቱን በጽኑ ያወግዛል::

- ለደረሰው የህይወት ጥፋት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት ተጠያቂ የሆኑት ግለሰቦች ለፍርድ እንዲቀርቡና መንግስት የዜጎችን የህይወት፣ የአካል ደህንነትና የንብረት መብቶችና ነጻነቶች በማስጠበቅ በኩል ያለበትን ህገመንግስታዊ ግዴታ በአግባቡ እንዲወጣ ኢሰመጉ በድጋሚ ይጠይቃል::

- በግፍ ለተገደሉ ግለሰቦች ቤተሰቦች፣ እንዲሁም ለቆሰሉና ንብረታቸውን ለተዘረፉ ወይም ለወደመባቸው ሁሉ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈላቸው ኢሰመጉ ይጠይቃል::

- በመጨረሻም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው በሁለቱ ብሄረሰብ አባላት መካከል ግጭት ሲፈጠር የመጀመሪያ ጊዜው ባለመሆኑ ለተደጋጋሚ ግጭት

መነሻ የሆኑት መሰረታዊ ምክንያቶች ተጣርተው ዘላቂ መፍትሔ እንዲፈለግላቸው ኢሰመጉ ይጠይቃል።

በተጨማሪም ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የኢትዮጵያ መንግስት ለደረሰው የህይወት መጥፋት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት ተጠያቂ የሆኑትን ግለሰቦች ለፍርድ እንዲያቀርብና ለዜጎች የህይወት፣ የአካል ደህንነትና የንብረት መብቶችና ነጻነቶች በቂ ጥበቃ እንዲያደርግ የበኩላችሁን ግፊት ታደርጉ ዘንድ ኢሰመጉ ይጠይቃል።
ግልባጭ

- **ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈጉባኤ
  ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0900
  ስልክ (251-1) 1241013
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ክቡር አቶ ደግፌ ቡላ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ
  ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0722
  ስልክ (251-11) 124 2301
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኘሬዚዳንት
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1438፣ ፋክስ (251-11) 155 2020
  ስልክ (251-11) 551 8850
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020
  ስልክ (251-11) 122 6767
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ክቡር አቶ ሲራጅ ፈጌሣ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0000
  ስልክ (251-11) 552 0000
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0874
  ስልክ (251-1) 551 5099
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ክቡር ዶ/ር መሐመድ ያሲን**
  *የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 101769፣ ፋክስ (251-11) 551 3642*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ፍቅሩ ኛካል**
  *የደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 18፣ ፋክስ (251-46) 220 1950*
  *አዋሳ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-11) 645 9290*
  *ስልክ (251-1) 645 9228*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አባይ ተክሌ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ዋና እንባ ጠባቂ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-11) 645 9229*
  *ስልክ (251-11) 663 5090፣ 663 5363*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*